# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

ቀን: **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ:** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

## የእሁድ 1:30 ጸሎት

እሁድ ልክ 1:30 ላይ ተገናኝተን በጸሎት እንድንተጋ ቤተ ክትርስትያን አጥብቃ ታሳስባለች። በተከታታይ በዚህ ሰአት በእግዚአብሔር ፊት የምንጸልይባቸው ጉዳዮች ስላሉን ልክ በሰዓቱ እንድንገኝ እናሳስባለን።

## የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




"ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።"
(ዮሐ. 14:27)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**March 3, 2019** | **የካቲት 24፤ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................ | እህት አመለ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወ/ም ረድኤቱ ካሳ |
| ቃል ............. | እህት ሰናይት ከበደ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

“ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ” በማለት የተቀኘው።” (ዕም. 3:17-18)።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## የእግዚአብሔርን መንግሥት መፈለግ—2

*“ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” (ማቴ. 6:33)*

ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 14 ቁጥር 17 ላይ እንደገለጸት "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት።” ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግስት አሁን በመካከላችን የመንግስቱ ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ ሲገለጽ በስራ ላይ ነች ማለት ነው። ባለፈው ሳምንት የመንግስቱን ጽድቅ ተመልክተናል። ዛሬ በመግስቱ ሰላምና ደስታ ላይ እናተኩራለን።

የእግዚአብሔር መንግስት ወንጌል ሰላም ይሰጣል። ጌታ ኢየሱስ በቃሉ “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም” ብሎናል (ዮሐ. 14:27)። ከቃሉ እንደምናስተውለው ሁለት አይነት ሰላም አለ። አለም የሚሰጠው በጊዚያዊ ነገሮችን ላይ የተመሰረተ ሰላም አለ፤ ደግሞም ጌታ የሚሰጠው ሰላም አለ። አለም የሚሰጠው ሰላም ውጪያዊ ነው። ከውጭ ባሉ ነገሮች ሁኔታ የሚወሰን ነው። የጌታ ሰላም ግን ከውስጥ የሆነ ሰላም ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእርጋታ እንድንቀመጥ የሚያደርገን የእግዚአብሔር ሰላም ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔር ሰላም በአለም እንዳለው ሰላም የነውጥ አለመኖር ብቻ ሳይሆን ዙሪአችን ነውጥ ቢኖርም እንኳ በእርጋታ መቀመጥ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሰላም ሲኖረን ልባችን አይታወክም፣ አይፈራም። ስለዚህ ነው ዘማሪው “ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም” ያለው (መዝ. 46፡2)። የሰላማችን ምንጭ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። በማንኛውም ሁኔታ በጸሎትና በልመና ከምስጋናም ጋር ወደ እርሱ ስንቀርብ እርሱ አእምሮን ሁሉ በሚያልፍ ሰላም ልባችንና ሃሳባችንን ይጠብቃል (ፊል. 4:7)። በመከራ መኃል፣ በችግር መኃል፣ በነውጥ መኃል አዕምሮአችን በሰላም የተጠበቀ ነው። እውነተኛ ሰላምና እረፍት ያለው የሰላም አለቃ ከሆነው ከጌታ ዘንድ ብቻ ነው። ወደ ህይወታችን ስንጋብዘው “ሰላም ለናንተ ይሁን” ብሎ በሰላሙ ያሳርፈናል። የግዚአብሔር ሰላም ልብን ይጠብቃል፤ የእግዚአብሔር ሰላም አእምሮን ያሳርፋል። ክርስቶስ ኢየሱስ ሸክማቸው የከበደውን ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ በሰላሙ ያሳርፋል።

መንግስቱን ስንፈልግ እግዚአብሔር ደስታን ይሰጠናል። ሰዎች በሚያገኙት ነገር ለተወሰነ ጊዜ ደስ ሊላቸው ይችላል። ነገር ግን በብዙ ጥረትና ድካም የተገኘ ነገር ለጊዜው ደስ ቢያሰኝም እንኳን ወረቱ ሲያልፍ በሌላ ምኞት ይተካና ያመጣው ደስታ ይደበዝዛል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ለመደሰት ሲሉ የተለያየ ሱስና የሃጢያት ልምምድ ውስጥ ይገባሉ። ነገር ግን ይህም ቢሆን ለጊዜው የሚሰጠው ደስታ ሲያልፍ ትርፉ ጸጸትና ራስ ምታት ይሆናል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ደስታ ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው። ደስታው ከውስጥ የሚወጣ እንጂ በውጪ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ አይደለም። ደስታችን መሰረቱ የሚመጡና የሚሄዱ ጉዳዮች ሳይሆኑ እግዚአብሔር እራሱ ነው። ለዚህ ነው እምባቆም “ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ” በማለት የተቀኘው (ዕም. 3:17-18)። እምባቆም በውጫዊ ነገሮች መጉደል ተናውጦና ደስታ ርቆት ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርን በክብሩ ከተመለከተ በኋላ ደስታ ምንጩ እግዚአብሔር እንጂ የነገሮች መሙላትና መጉደል እንዳልሆነ ተረዳ። እግዚአብሔር ደስታን ያልሰጠው ሰው ሁሉ ሞልቶትም እንኳ እርካታን ያጣል። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ “ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሰ ማን ነው?” (መክ. 2:25) የሚለን። ከርሱ ውጪ ደስታ የለም። ንጉስ ሰለሞንም ሁሉን ፈትኖ ደስታን ከሰበሰበው ሃብት፣ ጥበብ፣ ዝናና ተድላ ውስጥ ቢያጣት ጊዜ እግዚአብሔር “ደስ ለሚያሰኘው ሰው ጥበብንና እውቀትን ደስታንም ይሰጠዋል” (መክ. 2:26) በማለት የእውነተኛ ደስታ ምንጩ እርሱ እንደሆነ ተናገረ። ሰው ብዙ የሚደክመው ለመደሰት ነው ነገር ግን ለሰው የውስጥ ደስታን የሚሰጠው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የግዚአብሔር መንግስት በመካከላችን ስትሰራ የእግዚአብሔር ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ ይገለጣል።